# የስራ አጥነት ኢንሹራንስ(UI)

# መብትዎን ይወቁ!

## የስራ አጥነት ኢንሹራንስ(UI) ምንድን ነው?



የስራ አጥነት ኢንሹራንስ (Unemployment Insurance (UI)) ያለእርስዎ ጥፋት ከስራ ከተሰናበቱ ወይም የስራ ሰዓትዎ ከተቀነሰብዎ የሚሰጥዎ ሳምንታዊ የገንዘብ ድጎማ ነው። በሳምንት ከ $50 እስከ $444 ድረስ ያገኛሉ (በሚሰሩበት ሰዓት ከሚያገኙት ግማሽ የሚያህለውን)። UI እስከ 26 ሳምንታት ያህል ማግኘት ይችላሉ።

## UI ማግኘት እችላለሁኝ?

ዲሲ ውስጥ UI ለማግኘት፣ እነዚህ **ሁሉም** ነገሮች እውነት መሆን አለባቸው:-

- ☐ ዲሲ ውስጥ የሰሩ። *ዲሲ ውስጥ መኖር አያስፈልጎትም።*
- ☐ ስራዎን ከማጣትዎ በፊት በቂ ገንዘብ ያገኙ መሆን አለብዎ(*ባለፈው ዓመት ውስጥ ቢያንስ $1,900 እና ቢያንስ በአንድ ሩብ ዓመት ውስጥ $1,300*)። እዚህ የበለጠ ይወቁ https://does.dc.gov/service/claimant-eligibility/.
- ☐ ለስራ ቀጣሪ የሰሩ መሆን አለብዎ። *በራስዎ የ ሚሰሩ ከሆነ ወይም በግል የሚሰራ ኮንትራክተር ከሆኑ፣ መደበኛውን UI ማግኘት አይችሉም (ነገር ግን PUA ሊያገኙ ይችላሉ)። PUA ን በተመለከተ የሌጋል ኤድ በራሪ ጽሑፍን ይመልከቱ።*
- ☐ ከብቃት ማነስ ሳይሆን ምክንያት ባለው ሁኔታ ስራዎን ካጡ ወይም ከለቀቁ። *ማብራሪያውን ቀኝ ላይ ይመልከቱ።*
- ☐ *ሥራ መስራት የሚችሉ እና ለሥራ ዝግጁ ከሆኑ።*

***UI ማግኘት እንደማይችሉ እርግጠኛ ከሆኑ፣ ለማንኛውም ማመልከት ተመራጭ ነው!***

## የአሜሪካ ዜግነት የለኝም። UI ማግኘት እችላለሁኝ?

**አዎ፣** በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የስራ ፈቃድ እስካለዎት ድረስ። በሚያመለክቱበት ሰዓት የስራ ፈቃድዎን ይያዙ።

የስራ ፈቃድ ከሌለዎ፣ ወይም ሕጋዊ የመኖሪያ ፈቃድ ከሌሎት፣ UI ማግኘት አይችሉም።

## UI እንዳላገኝ የሚያደርገው ምን ዓይነት የስራ ማጣት ነው?

**ከስራ መባረር።** "አላግባብ ባህሪ" የተነሳ ከስራ የተባረሩ ከሆነ፣ ሙሉውን UI ጥቅማጥቅሞች ማግኘት አይችሉም። አላግባብ ባህሪ ማለት በስራ ላይ የተሳሳተ ነገር እንደሚሰሩ እያወቁ የፈጸሙት ነው።

**ከስራ መልቀቅ።** በአጠቃላይ፣ ከስራ ለመልቀቅ "ጥሩ ምክንያት ከሌሎት ***በስተቀር*** በገዛ ፈቃድዎ ከስራ ከለቀቁ UI አያገኙም።

"ጥሩ ምክንያት" ማለት ከስራዎ ጋር የሚያያዝ በጣም ጥሩ ምክንያት ማለት ነው(*አስተማማኝ ያልሆነ የስራ ሁኔታ፣ የዘር አድሎ፣ ለባለትዳር ስራ ከተማ መቀየር፣ የታመመ ወይም አካለስንኩል ለሆነ የቤተሰብ ዓባል መንከባከብ ካስፈለገ፣ ስራዎ በሽታዎን ወይም አካለስንክልናዎን የከፋ ካደረገው፣ ስራ ከመልቀቅዎ በፊት ለቀጣሪዎ የዶክተር ማስታወሻ እስከሰጡት ድረስ)*።

## ከኮቪድ-19 ጋር የሚያያዙ ልዩ ጥቅማጥቅሞች አሉ?

**አዎ።** እነዚህ ጥቅማጥቅሞች የሚቆዩት እስከ ሴፕቴምበር 4፣ 2021 ሲሆን በእዚህ ሊያግዙት ይችላሉ:-

- UI ጥቅማጥቅሞችን ሊያገኙባቸው የሚችሉትን ጊዜ በማራዘም (*የወረርሽኝ የድንገተኛ ጊዜ የስራ አጥነት ካሣ (Pandemic Emergency Unemployment Compensation) ወይም PEUC)*
- በሳምንት ተጨማሪ $300 ጥቅማጥቅሞችን ይሰጦታል (*የፌደራል የወረርሽኝ ስራ አጥነት ካሣ (Federal Pandemic Unemployment Compensation)፣ ወይም FPUC)*
- መደበኛ UI ማግኘት ለማይችሉ አንዳንድ ሰዎች ጥቅማጥቅሞችን መስጠት (*የወረርሽን የስራ አጥነት ድጋፍ (Pandemic Unemployment Assistance)፣ ወይም PUA)*

## እንግሊዘኛ በደንብ የማልናገር ከሆነ ማመልከት እችላለሁኝ?

**አዎ።** ሕግ የሚለው መንግስት በእርስዎ ቋንቋ ሊያግዞት ይገባል ነው። የሚፈልጉትን ኤጀንሲ በእርስዎ ቋንቋ እገዛ እንደሚሹ ይንገሯቸው።

***UI ላይ እንዴት ማመልከት እንደሚችሉ ለማወቅ ቀጣዩ ገጽ ላይ ይሂዱ።***

**እገዛ ይፈልጋሉ?** (202) 628-1161 ላይ ሌጋል ኤድ ጋር ይደውሉ ወይም ወደዚህ ይሂዱ https://www.legalaiddc.org/online-intake/።

## UI ላይ እንዴት ማመልከት እችላለሁኝ?

UI ከዲሲ የቅጥር አገልግሎቶች መምሪያ (DC Department of Employment Services) (DOES) ጋር በመሄድ ያመልክቱ። በስልክ **202-724-7000** ላይ በመደወል ወይም አንላይን እዚህ ላይ ማመልከት ይችላሉ **dcnetworks.org**።

## UI ላይ ለማመልከት የመጨረሻ ቀነ ገደብ አለው?

አይ፣ ምንም ዓይነት መደበኛ ቀነ ገደብ የለውም። ሆኖም ግን፣ ስራዎን ካጡ በኋላ ለማመልከት ብዙ ጊዜ ከቆዩ ደሞዝዎ "ጊዜው ያልፍበታል"።

**ስራዎን ካጡ በኋላ በተቻለ ፍጥነት UI ላይ ማመልከት በተለምዶ ተመራጭ ነው።** ጥቅማጥቅሞች የሚያገኙት UI ካመለከቱበት ቀን ጀምሮ ሲሆን፣ ከስራ የተሰናበቱበት የመጨረሻ ቀን ጀምሮ አይደለም።

## ጥቅማጥቅሞቹ መሰጠት እስከሚጀምሩ ምን ያህል ጊዜ ይፈጃሉ?

DOES ማመለከቻ በገባ **በሶስት ሳምንት ጊዜ ውስጥ** ምላሽ ለመስጠት ይሞክራል። ከ DOES ለአራት ሳምንት ወይም ከዚያ በላይ ምንም ዓይነት ደብዳቤዎች፣ ስልክ ጥሪዎች፣ ወይም ኢሜይሎች (በኢሜይልዎ ውስጥ ያሉ አይፈለጌ መልዕክቶች ጭምር) ያላገኙ ከሆነ፣ DOES ን በስልክ (202) 724-7000 ወይም በዚህ ኢሜይል ያግኙ uiescalations@dc.gov።

## ለ UI ብቁ ከሆንኩኝ በኋላ ምን ይፈጠራል?

በየሳምንቱ፣ አንላይን፣ በስልክ፣ ወይም በደብዳቤ(ደብዳቤ አይመከርም) ላይ ሳምንታዊ የይገባኛል ጥያቄ ካርድ ማስረከብ አለብዎ። እነዚህ ካርዶች ላይ፣ ማለት ያለብዎ:-

- *ሥራ መስራት የሚችሉ እና ለሥራ ዝግጁ እንደሆኑ፣ **እና***
- ለስራ በንቃት እየፈለጉ እንደሆነ (ቢያንስ ሁለት ጊዜ ያህል) እና የቀረበልዎን ስራ እንደሚቀበሉ።

**የይገባኛል ካርዶችዎን የማይሞሉ ከሆነ ወይም መስራት የማይችሉ እና የማይፈልጉ ከሆነ እና ስራ የማይፈልጉ ከሆነ፣ UI ማግኘት አይችሉም።**

## UI የተከለከልኩኝ ከሆነስ?

UI ከተከለከሉ፣ የይገባኛል ጥያቄ ገምጋሚው ውሳኔ በተሰጠበት 15 ቀናት ውስጥለአስተዳደር ጉዳዮች ሰሚ ቢሮ (Office of Administrative Hearings) (OAH) ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ (ምንም እንኳን ቀነ ገደቡ በጣም አሳማኝ ምክንያት ካሎት ሊራዘም ይችላል)። ይግባኝ ለመጠየቅ ሶስት ቅደም ተከተሎች አሉ።

**ቅደም ተከተል 1፡-** አንላይን እዚህ ላይ የይገባኛል ጥያቄውን ያግኙ https://oah.dc.gov/publication/ui-request-hearing-appeal-determination-claims-examiner-involving-unemployment-benefits ወይም OAH ን በ (202) 442-9094 ላይ ይደውሉ።

**ቅደም ተከተል 2፡-** የይግባኝ ቅጹን ይሙሉ።

**ቅደም ተከተል 3፡-** ከእነዚህ መንገዶች ውስጥ በአንዱ ቅጹን ይሙሉ:-

- በዚህ **ኢሜይል** ይላኩት oah.filing@dc.gov.
- የአስተዳደር ሰሚዎች ቢሮ (Office of Administrative Hearings)፣ 441 Fourth Street NW, Suite 450N, Washington, DC 20001 **በአካል በመገኘት ያምጡት**። *የቅጹን ቅጂ ያስቀምጡ።*
- ከላይ የተጠቀሱት አድራሻዎች ላይ **በደብዳቤ** ይላኩት። *የቅጹን ቅጂ ያስቀምጡ። የላኩበትን ቀን ጽፈው ያስቀምጡ። **ደብዳቤ አይመከርም።***

የይግባኝ ጥያቄውን ለመከታተል፣OAH ን በ (202) 442-9094 ላይ ደውለው ማግኘት ይችላሉ።

> መደበኛ UI የተከለከሉ ከሆነ፣ PUA ማግኘት እንደሚችሉ ይመልከቱ እና ያረጋግጡ። ማመልከቻውን እዚህ ላይ ያግኙ https://dcdoes.force.com/PUAForm/s/?language=en_US.

***እገዛ ይፈልጋሉ?*** (202) 628-1161 ላይ ሌጋል ኤድ ጋር ይደውሉ ወይም ወደዚህ ይሂዱ https://www.legalaiddc.org/online-intake/።